የከ/መ/ቁ 283664
ህዳር 03 ቀን 2013 ዓ/ም

ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት
ልደታ ምድብ 4ኛ ንግድ ችሎት

ዳኛ፡- መካ ነስሩ

ከሣሽ፡- ወ/ሮ እየሩሳሌም ለማ - ተወካይ ዮናስ ሰለሞን ቀረቡ
ተከሣሽ፡- አቶ ዘላለም ደቻሳ - አልቀረቡም
መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የከሣሽ ተወካይ በአጭር ሥነ-ሥርዓት ታይቶ እንዲወሠን በየካቲት 26 ቀን 2012 ዓ.ም ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ከሳሽ እና ተከሳሽ መካከል ንግድ ስራ ግንኙነት የነበረን ሲሆን በዚህ የንግድ ግንኙነት መሰረት ከሳሽ ለተከሳሽ ለሰጠሁት ብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺህ ብር/ ለመተማመኛ የሚሆን ተከሳሽ በቼክ ቁጥር AF5042500 በህዳር 17 ቀን 2012 ዓ/ም በተፃፈ ብር 300,000 /ሦስት መቶ ሺህ ብር/ ከዓባይ ባንክ መስቀል ፍላወር ቅርንጫፍ እንድቀበል ቼክ ከቆረጠልኝ በኋላ በተፃፈው ቼክ መሰረት ክፍያውን ለመቀበል ወደ ባንኩ ስሄድ የተከሳሽ አካውንት በቂ ስንቅ የሌለው እና የተዘጋ በመሆኑ ክፍያውን ሊፈፅም እንደማይችል ባንኩ በየካቲት 11 ቀን 2012 ዓ/ም ማረጋገጫ ሰቶኛል፡፡በመሆኑም ተከሣሽ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲሁም በዚህ ክስ ምክንያት ያወጣሁትን ወጪዎች ጨምረው እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ በማስረጃነትም የቼኩን ኮፒ እና ባንኩ የሠጠውን ማረጋገጫ አቅርዋል፡፡
ተከሣሽ በህጉ አግባብ ጥሪ ቢደረግላቸውም በአስር ቀናት ውስጥ መከላከያ ማስፈቀጃ ያላቀረቡ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ የመከላከል መብታቸውን አልፎታል፡፡
ፍርድ ቤቱም የከሳሽ ክስ እና ማስረጃ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡
ከሣሽ ክስ ያቀረበው ተከሣሽ እንዲከፈልበት የሠጡኝ ቼክ ለክፍያ ለከፋዩ ባንክ ቀርቦ ሳይከፈልበት የተመለሰ በመሆኑ በቼኩ ላይ የተፃፈውን ገንዘብ ተከሣሽ ሊከፍሉኝ ይገባል በማለት ሲሆን ለክሱ መነሻ የሆነው ቼክ በተከሣሽ ስም የወጣ መሆኑንና ይህ ቼክ ለክፍያ ቀርቦ ባንኩ የእንቢታ ማስታወቂያ በመስጠት ሳይከፈልበት የተመለሰ መሆኑን የሚያስረዱ ማስረጃዎች ቀርበዋል፡፡
ከሣሽ ለክሱ መሠረት ያደረጉት ጉዳይ ቼክ ሲሆን ቼክ ደግሞ በንግድ ህጋችን እንደ ንግድ ወረቀት ይቆጠራሉ ተብለው በን/ህ/ቁ 732/2/ ስር ከተዘረዘሩት የንግድ ወረቀቶች አንዱ ነው፡፡ ቼክ ከንግድ ወረቀቶች ውስጥ አንዱ ቢሆንም ከሌሎች የንግድ ወረቀቶች የሚለይባቸው ልዩ ባህሪያት ያሉት፣ ገንዘብን ተክቶ በስፋት አገልግሎት እየሠጠ ያለ፣ በንግድ ህጉ እንዲሁም በሌሎች ህጐቻችን ልዩ ጥበቃ የተሠጠው የንግድ ወረቀት ሲሆን ከነዚህ ልዩ ባህሪያት አንዱ ቼክ እንደቀረበ የሚከፈልበት የንግድ ወረቀት መሆኑ ነው፡፡ ይህም በን/ህ/ቁ 854 ስር ተመልክቷል፡፡ የቼኩ አምጪ / Drawee / ቼኩን ለክፍያ ለከፋዩ ባንክ /Payee/ አቅርቦ ቼኩ ሳይከፈልበት ከተመለሰ የቼኩ አውጪ /Drawer/ ስለ ቼኩ አከፋፈል ዋስ በመሆኑ እና ገንዘቡን የመክፈል ሀላፊነት ያለበት በመሆኑ በቼኩ ላይ የተፃፈውን ገንዘብ የቼኩ አውጪ እንዲከፍለው መጠየቅ ይችላል፡፡ ይህም በን/ህ/ቁ 840 ፣ 868 ፣ 881 /1/ ስር ተመልክቷል፡፡
ከዚህ ላይ ደግሞ ተከሳሽ የቼኩ አውጪ በመሆናቸው እና ይህ እንዲከፈልበት የወጣው ቼክም ሳይከፈልበት የተመለሰ በመሆኑ ተከሣሽ በን/ህ/ቁ 840 መሠረት ገንዘቡን የመክፈል ሀላፊነት አለባቸው፡፡ የቼኩ አውጪ ከዚህ ኃላፊነት ሊድን የሚችለው ማለትም በቼኩ ላይ የተፃፈውን ገንዘብ ለቼኩ አምጪ የመክፈል ኃላፊነት የማይኖርበት፣ ቼክን መሠረት አድርጐ ለቀረበ ክስ

በቼኩ አምጪ ላይ ሊቀርቡ ይችላሉ ተብለው በህጉ ተለይተው እና ተወስነው በን/ህ/ቁ 717 ስር የተቀመጡትን መከላከያ ምክንያቶች ያቀረበ፣ ይህን መከላከያ ምክንያቱንም ያስረዳ ሲሆን ነው፡፡ ይህ መከላከያም በን/ሕ/ቁጥር 717/1//3/፣ 849፣ 850 ስር የተቀመጠውን አይነት ከቼኩ አምጪ ጋር ያለውን የግል ግንኙነት መሠረት ያደረገ /Personal Relation Ship Defence/ ወይም በን/ሕ/ቁጥር 717/1/2/ ስር የተመለከቱት አይነት ከቼኩ አወጣጥ፣ ፎርም፣ የተፃፉ ቃላትና ፊርማ መሠረት ያደረጉ ቼኩን የሚመለከቱ መከላከያዎች /Real Defence/ ያቀረበ እና ይህንም መከለከያውን ያስረዳ ሲሆን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተከሣሽ በቼኩ ላይ የተመለከተውን ገንዘብ የከፈሉ ስለመሆኑ ወይም ሌላ የማይከፍሉበት ምክንያት ያለ ስለመሆኑ በህጉ መሠረት ያቀረቡት መከላከያ የለም፡፡ በአጭር ሥነ-ሥርዓት ታይቶ እንዲወሠን ባቀረበው ክስ ተከሣሹ መከላከያ ካላቀረበ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለከሣሽ እንዲከፍል ሊወሠን እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 285/2/ ስር ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም ተከሣሽ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ብር 300,000 /ሦስት መቶ ሺህ ብር/ ለከሣሽ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. ተከሳሽ ክስ የቀረበበት ገንዘብ ውስጥ ብር 300,000 /ሦስት መቶ ሺህ ብር/ ክስ ከቀረበበት የካቲት 26 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚጠናቀቅ ጊዜ ድረስ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለከሣሽ እንዲከፍል ተወስኗል፡፡

2. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር ምክንያት የወጣ ወጪ ወጪና የደረሰ ኪሳራ ለዳኝነት የከፈሉትን ብር 5,850፣ ለቴምብር ቀረጥ ብር 30፤ የትራንስፖርት እና የፅሕፈት አገልግሎት በቁርጥ ብር 1,200 በድምሩ 6,080 (ስድስት ሺህ ሰማንያ ብር) ተከሣሽ ለከሣሽ እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

ይግባኝ ለጠየቀ መዝገቡ ተገልብጦ ይሠጠው፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የዳኛ ፊርማ አለበት፡፡